Ontario

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

# የማህበራዊ ስነሕዝብ መረጃ ለመሰብሰብ፥ ለመጠቀምና ገልጾ ለማውጣት ፈቃድ

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የኮቪድ-19 ክትባት ከሚወስዱ ሰዎች ማህበራዊ የስነሕዝብ መረጃ እየሰበሰበ ነው። ይህም የዘር፥ ጎሳ፥ ገቢ፥ የቤተሰብ መጠንና ቋንቋ መረጃን ያካትታል።

ይህን መረጃ ለሚኒስቴሩ ለማሳወቅ ከወሰኑ፥ ሚኒስቴሩ ክትባቶችን በኦንታሪዮ ውስጥ እንዴት እንደሚያሰራጭና እንደሚያስተዋውቅ ለማቀድ እንዲሁም በሕግ ለሚፈቀዱና አስፈላጊ ለሆኑ ለሌሎች ጉዳዮች ይጠቀምበታል።

ሚኒስቴሩ መረጃውን በመጠቀም ለሕዝብ የሚቀርቡ ሪፖርቶች ያዘጋጃል። እነዚህ ሪፖርቶች እርስዎን ለመለየት የሚያገለግል ማንኛውንም መረጃ አያካትቱም። ሚኒስቴሩ ይህ መረጃ በኃላፊነት ጥቅም ላይ መዋሉንና የሰዎችን ግለኝነት ማክበሩን ያረጋግጣል።

ማንኛውም የሚሰጡት መረጃ በCOVax (ኮቫክስ) ሥርዓት ውስጥ የሚቀመጥ ሲሆን በክትባት ክሊኒኮች ውስጥ ያሉ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ሊያገኙት ይችላሉ። COVax በሚኒስቴሩ ጥበቃና ቁጥጥር ሥር ያለ የጤና መዝገብ ሥርዓት ነው።

**ይህን መረጃ የሚሰጡት በፈቃደኝነት ነው።**

ይህን መረጃ መስጠት ካልፈለጉ ግዴታ የለብዎትም። ፈቃድ ስላልሰጡ የኮቪድ-19 ክትባት ወይም ማንኛቸውንም ሌሎች አገልግሎቶች አይነፈጉም። ጥያቄዎቹን በሙሉ፥ በከፊል ወይም ለየትኞቹም መልስ መስጠት ይችላሉ።

መረጃዎን ከሰጡ በኋላ ወደፊት ጥቅም ላይ ስለመዋሉ ሐሳብዎን ከቀየሩ፥ ሚኒስቴሩን ተገናኝተው የማህበራዊ ስነሕዝብ መረጃዎ ጥቅም ላይ እንዳይውል ወይም ተገልጾ እንዳይወጣ መጠየቅ ይችላሉ።

ይህን ለማድረግ ሚኒስቴሩ ጋር በConsentWD@ontario.ca ኢሜል ማድረግ ይችላሉ።

መረጃዎን ለሚኒስቴሩ ለመስጠት ፈቃድ ይሰጣሉ?

☐ **ለተገለጹት ዓላማዎች እንዲውል የማህበራዊ ስነሕዝብ መረጃዬን ለማቅረብ ፈቃደኛ ነኝ።**

Ontario

| |
|---|
| **ጎሳዎ ወይም ባህላዊ ምንጭዎ(ጮችዎ) ምንድነው?**<br>ለምሳሌ፡- ካናዳዊ፥ ቻይናዊ፥ ምሥራቅ ሕንድ፥ እንግሊዝ፥ ጣልያን፥ ፊሊፒናዊ፥ ስኮቲሽ፥ አይሪሽ፥ ፖርቹጊዝ፥ ጀርመናዊ፥ ፖላንዳዊ፥ ደች፥ ፈረንሳዊ፥ ጃማይካዊ፥ ፓኪስታናዊ፥ ኢራናዊ፥ ስሪላንካናዊ፥ ኮሪያዊ፥ ዩክሬንያናዊ፥ ሊባኖሳዊ፥ ጉያናዊ፥ ሶማሌ፥ ኮሎምቢያዊ፥ አይሁድ፥ ወዘተ. |

| **ከሁሉም የተሻለ የሚገልጽዎ የትኛው ነው?** የሚመለከትዎ ላይ ሁሉ ምልክት ያድርጉ። | |
|---|---|
| **የዘር ምድቦች** | **መግለጫ/ምሳሌዎች** |
| ☐ ጥቁር | አፍሪካዊ፥ አፍሮ ካሪቢያናዊ፥ አፍሪካን ካናዳዊ ዝርያ |
| ☐ ምሥራቅ እስያዊ | ቻይናዊ፥ ኮሪያዊ፥ ጃፓናዊ፥ ታይዋናዊ ዝርያ |
| ☐ ደቡብ ምሥራቅ እስያዊ | ፊሊፒናዊ፥ ቬዬትናማዊ፥ ካምቦዲያዊ፥ ታይላንዳዊ፥ ኢንዶኔዚያዊ፥ ሌላ የደቡብ ምሥራቅ እስያ ዝርያ |
| ☐ ላቲኖ | ላቲን አሜሪካዊ፥ ሂስፓኒክ ዝርያ |
| ☐ ማዕከላዊ ምሥራቅ | አረብ፥ ፐርሻዊ፥ ምዕራብ እስያ ዝርያ፥ ለምሳሌ አፍጋናዊ፥ ግብጻዊ፥ ኢራንያዊ፥ ሊባኖሳዊ፥ ቱርካዊ፥ ከርዲሽ፥ ወዘተ. |
| ☐ ደቡብ እሲያዊ | ደቡብ እስያዊ ዝርያ፥ ለምሳሌ ምሥራቅ ህንድ፥ ፓኪስታናዊ፥ ባንግላዴሻዊ፥ ኢንዶ ካሪቢያናዊ፥ ወዘተ. |
| ☐ ነጭ | የአውሮፓ ዝርያ |
| ☐ ሌላ የዘር ምድብ | እባክዎን ይግለጹ፡- |

| | | |
|---|---|---|
| **ባለፈው ዓመት ከግብር በፊት የነበረው አጠቃላይ የቤተሰብ ገቢዎ ስንት ነበር?**<br>አንዱን ይምረጡ። | ☐ $0-$29,999<br>☐ $30,000 - $49,999<br>☐ $50,000 - $69,999<br>☐ $70,000 - $99,999 | ☐ $100,000 - $149,999<br>☐ $150,000 ወይም ከዛ በላይ<br>☐ አላውቅም<br>☐ መልስ ባልሰጥ እመርጣለሁ |

| | | |
|---|---|---|
| **ቤትዎ ውስጥ እራስዎን ጨምሮ ስንት የቤተሰብ አባሎች በመደበኛነት ይኖራሉ?** | ☐ 1 ☐ 2 ☐ 3 ☐ 4 ☐ 5 ☐ 6<br>ሌላ፡-<br>☐ አላውቅም<br>☐ መልስ ባልሰጥ እመርጣለሁ | |
| **በልጅነትዎ በቤትዎ ውስጥ መጀመሪያ የተማሩትና አሁንም የሚረዱት ቋንቋ ምንድነው?** እባክዎን ይግለጹ፡- | | |
| **በየትኛው የካናዳ ኦፊሲዮላዊ ቋንቋዎች እንግሊዝኛ ወይም ፈረንሳይኛ በይበልጥ ይግባባሉ?** | ☐ ፈረንሳይኛ<br>☐ እንግሊዝኛ<br>☐ በሁለቱም እንግሊዝኛም ፈረንሳይኛም | ☐ አላውቅም<br>☐ በየትኛውም<br>☐ መልስ ባልሰጥ እመርጣለሁ |